


## የሸንጎ የሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ መልእክት

ከአርባ ዓመታት በፊት በወርሃ የካቲት ነበር የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ተነሳስቶ ለባላባታዊው ሥርዓት አልገዛም ብሎ ከበትረ-መንግሥቱ እንዲወርድ ያስገደደው። አለመታደል ሆኖ ሕዝቡ የተነሳበት የለውጥ እንቅስቃሴ ተቀልብሶ አምባገነኑ ደርግ በሥልጣን ኮርቻ ላይ እንዲቀመጥ ሆነ። ደርግ የሕዝቡን ጥያቄ ሊመልስ የሚችል ኃይል ካለመሆኑም በላይ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲል በሀገራችን ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የንፁሃንን ዜጎችን ደም በጠራራ ፀሐይ በአደባባይ እንደጎርፍ አፈሰሰ። ሕዝብን በጠብመንጃ ኃይል ረግጦ ይገዛ ስለነበረና ሕዝባዊ ድጋፍ ስላልነበረው እንደማንኛውም አምባገነን አገዛዝ አይወድቁ አወዳደቅ ወድቆ የታሪክ ትቢያ ሆነ። ሕዝብ መሠረታዊ ለውጥን ቢፈልግም፤ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመሠረት ቢመኝም፤ ያልተሸራረፉ የሕዝብ መብቶች እንዲከበሩ ቢሻም ለሁለተኛ ጊዜ በ1983 ዓ. ም መልካም አጋጣሚው አመለጠው። እንደደርግ ሁሉ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አፍኖ፤ የነፃው ፕሬስና የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትን እሥር ቤት በማጎር፤ ሕዝቡን ረግጦ የሚገዛ በህወሓት የሚመራው አገዛዝ እራሱን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጫነ። አምባገነኑ የህወሓት አገዛዝ የአፈና ስልቱን የበለጠ እያጠናከረ እነሆ 22 ዓመታትን አስቆጠረ።

የህወሓት/ኢህአዴግን አገዛዝ በሀገራችን ውስጥ ቀድሞ ከነበሩት መንግሥታት ለየት የሚያደርገው ኢትዮጵያዊ ፍቅር የሌለው፤ ዜጎችን በጎሣ በመከፋፈል በብሄረሰቦች ላይ የተመሠረቱ የክልል አስተዳደሮችን በመመሥረት ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳ መሆኑ ነው። ለሀገር ድንበር መከበርም ደንታ ስለሌለው ከ1200 ኪሎሜትር በላይ ርዝመት፤ ከ30 እስከ 50 ኪሎሜትር ስፋት ያለውን የሀገራችንን ለም መሬት ለጎረቤት ሱዳና አሳልፎ ለመስጠት ዝግጅቱ የተጠናቀቀ መሆኑን የዜና አውታሮች ዘግበዋል። በተጨማሪም በምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኘውን ለምና ድንግል መሬት የአካባቢውን ነዋሪዎች እያፈናቀለ በነፃ ሊባል በሚችል ደረጃ ለውጭ ባለሃብቶች በረጅም ጊዜ ኮንትራት መስጠቱ የሚታወቅ ነው። ይባስ ብሎ የሚመረተውን የእርሻ ውጤት በሀገር ውስጥ እንዲሸጡ እንኳን ግዴታ እንዳላስገባቸው ይታወቃል።

ይህ ለሀገርና ለወገን ፍቅር የሌለው አገዛዝ ሲገዛበት በነበረው ጎዳና እንዲቀጥል ከፈቀድንለት ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር መኖሯም አጠራጣሪ ይሆናል። ይሁን እንጂ እናቶቻችንና አባቶቻችን አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው የውጭ ጠላቶቸን አሳፍረውና አንድነቷን ጠብቀው ያስረከቡንን ኢትዮጵያችንን ስትፈራርስ ዝም ብለን ማየት የለብንም። ይህንን ሀገር አጥፊ አገዛዝ በተባበረ ክንድ ማስወገድ ወቅታዊና አንገብጋ ጥያቄ ነው። ይህንንም እውን ለማድረግ የፖለቲካ ድርጅቶች ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወቱ ይገባል።
የሕዝብን የቁጣ ማዕበል አቀናጅቶ በአንድ ላይ እንዲነሳ ማድረግ ከማንኛውም ለሀገርና ለወገን ጥቅም ከቆመ ድርጅት የሚጠበቅ ነው። በአንድነት የተነሳን ሕዝባዊ ኃይል ሊመክት የሚችል ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል እንደሌለ ከ40 ዓመታት በፊት በሀገራችን የፈነዳው የየካቲት አብዮት አረጋግጦልናል። ስለዚህ የፖለቲካ ድርጅቶች ተከባብረውና የትግል አንድነት ፈጥረው እንዲታገሉና እንዲያታግሉ ይጠበቅባቸዋል። ሕዝብ ደግሞ ደጋግሞ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" ብሎ የነገረን ቢሆንም በሀገራችን አንድነቷን የጠበቀች ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረት መሰባበር አማራጭ ባለመሆኑ ያለን አማራጭ አንድና አንድ ብቻ ነው፤ ይኸውም ተባብሮ መታገል። ለዚህም ነው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ የሚታገሉ ኃይሎች ሁሉ የትግል አንድነት ፈጥረው እንዲታገሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ጥሪት እያደረገ ያለው።

ከሃያ ሁለት ወራት የምሥረት ሂደት በኋላ ከ20 ወራት በፊት የተቋቋመው ሸንጎ አምስት የፖለቲካ ድርጅቶችን፤ ሰባት የሲቪክ ድርጅቶችንና በርካታ ታዋቂ ግለሰቦችን አቅፎ የሚጠበቅበትን ግዳጅ ለመወጣት እየጣረ ይገኛል። ሸንጎ ኅብረት፤ ኅብረት አሁንም ኅብረት ይላል፤ ሌላ አማራጭ የለምና። ስለዚህ ያልተደራጁ ወገኖች እንዲደራጁ፤ የተደራጁትም የድርጅታቸውን ህልውና ጠብቀው ሸንጎን እንዲቀላቀሉ፤ መቀላቀል የማይፈልጉትም ኅብረት ፈጥረው በጋራ እንዲታገሉ ሸንጎው ጥሪውን በድጋሚ ያቀርባል።

በሸንጎው መሠረታዊ አቋሞች ማለትም በሀገራችን ሉዓላዊነትና አንድነት መከበር፤ የሕግ የበላይነት መስፈን፤ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፤ በዜጎች መካከል ልዩነት ሳይኖር በሕግ ፊት በእኩልነት እንዲታዩና፤ አምባገነኑ አገዛዝ ተወግዶ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲተካ ከሚታገሉ ኃይሎች ጋር ሁሉ ሸንጎው በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጣል።

በመጨረሻም ሸንጎው የተያያዘውን የማሰባሰብ ሂደት ብሎም የተቃዋሚዎችን ጎራ አጠናክሮ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ምሥረታ የሚያደርገውን ትግል በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሁለንተናዊ ድጋፍ እንዲሰጡት አበክሮ ይጠይቃል።

## የሸንጎው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቀጠለ

የሸንጎው እንቅስቃሴ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ጥንካሬ እያገኘ በመጓዝ ላይ ይገኛል።

በፖለቲካው በኩል ባለፈው ሶስት ወራት ሸንጎው ያዘጋጃቸው ሁለት ታላላቅ ውይይቶች ተካሂደዋል። በዚህም መሰረት በአቶ አገሬ አዲስ እና በዶክተር ፍቃዱ አቅራቢነት በብሄራዊ እርቅ እና የቅራኔ አያያዝና

አፈታትን በሚመለከት ርዕስ ላይ ሰፊ ገለጻና ውይይት ተካሂዷል። በፌበርዋሪ 8፣ 2014 ደግሞ የድንበር ኮሚቴ አባላት የሆኑት ፕሮፌሰር አለምአንተና አቶ አገኘሁ ሰፊ ገለጻ ያቀረቡ ሲሆን በዛ ያለ ህዝብ በቴሌ ኮንፍረንስ እንዲሁም በቃሌ የፓልቶክ መወያያ ክፍል አማካኝነት ለማድመጥና የውይይቱ ተካፋይ ሊሆን ችሏል።
ተመሳሳይ በሆነ መልክ በዋና ዋና ሀገራዊ ጥያቄዎች ላይ የሚካሄደው ውይይት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

በዲፕሎማሲው እንቅስቃሴም በቅርቡ የአሜሪካን ምክር ቤት ለኢትዮጵያ የሚሰጥ እርዳታ ከሰብአዊ መብት መከበር አንጻር እየተመረመረ መሆን እንደሚገባው ያሳለፈውን ህግ በማንተራስ፣ ከሚመለከታቸው የኮንግረስ አባላት ጋር ሸንጎው ግንኙነት ያደረገ ሲሆን ቀጣይ በሆነ መልኩ በሀገራችን ውስጥ የሚካሄደውን ግፍ ለማብቃት መወሰድ ስለሚገባው ተጨባጭ እርምጃወችም ተግባራዊነት የሚያደርገው ስፊ እንቅስቃሴ ይቀጥላል። ይህ ጅምር በአሜሪካ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም መካሄድ ያለበት እና የሚቻል እንደሆነ ሸንጎው ይገነዘባል ለዚህም ይሰራል።

በሳውዲ አረቢያ በሚገኙ ወገኖቻችን ላይ በሀገሪቱ መንግስትና የጸጥታ ሀይል የደረሰውን አስከፊ የመብት ረገጣ በመቃወም የሸንጎ አባላቱና ደጋፊዎቹ እንቅስቃሴ በተጀመረበቸው ቦታወች ከሌሎች ጋር በማበር በልተጀመረባቸው ቦታወች ደግሞ አስፈላጊውን ግንባር ቀደም የማስተባበር ስራ በመስራት ሀላፊነተቸውን እነዲወጡ በመላው አለም ለሚገኙ አባላቱና ደጋፊዎቹ በሰጠው መመሪያ መሰረት የወገኞቻችንን ብሶት ለማስተጋባት ስፊ እና አመርቂ ስራ ተካሂዷል።በመካሄድም ላይ ነው።

የህዝብ ግንኙነት ስራችንን አጠናክረን የሸንጎውን እንቅስቃሴ ለህዝብ ለማሳወቅ የሸንጎው ባለስልጣናት በተለያዩ የመገናኛ መስኮች በመቅረብ ቃለ መጠይቅ ያደረጉ ሲሆን ፣ በሀገራችን ውስጥ የሚከሰቱ ሁኔታወችን በተመለከተም የሸንጎውን አመለካከትና አቋም በተከታታይ በመግለጫወች ከማሳወቅ አልቦዘነም።

የሸንጎው አመራር አባላት ከህዝብ ጋር በመገናኘት ቀጥተኛ ውይይት ለማድረግ በተወሰነው መሰረት የሸንጎው የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል እና የውጭ ጉዳይ ሀላፊ የሆኑት ዶክተር አክሎግ ቢራራ በፊበርዋሪ 15፣ 2014 በሳን ሆዜ ካሊፎርንያ እና ከአካባቢው ነዋሪ ጋር በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት ያደርጋሉ።

ተመሳሳይ ስብሰባወችን ባውሮፓና ባሜሪካ የተለያዩ ከተሞች፣ እንዲሁም በካናዳ ለማካሄድ ዝግጅቱ ቀጥላል።

## ይድረስ ለመለዮ ለባሹ

መለዮ ለባሽ የአገሩን ነጻነትና ዳር ድንበር ለማስከበር፣ የወገኑን ክብር አሳልፎ ላለመስጠት ህይወቱን ለመሰዋት ቆርጦ ዘብ የቆመ ዜጋ ነው። በአገራችን ታሪክ ውስጥ ሁሉም ዜጋ ከየአቅጣጫው በክተት አዋጅ ተጠራርቶ የአገሩን ህልውና ሲያስጠብቅ የኖረ መሆኑ ባይካድም እንደ አሁኑ በትጥቅ ተደራጅቶ አርበኝነትን እንደ ሙያ ቆጥሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ወታደር ሆኖ ደመወዝ ተቆርጦለት የተሰለፈው በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነመንግስት ነበር። ከዚያም በኋላ የተነሱ መሪዎች የአጼ ቴዎድሮስን ፈለግ በመከተል በሚችሉት መጠን ተቋሙን በማሳደግና በማሻሻል ለአሁኑ ደረጃ እንዲበቃ አድርገውታል። በተለይም በመጨረሻው ንጉስ ፣ በአጼ ሃይለስላሴ ዘመነ መንግስት አቅም በሚፈቅደው መጠን ፣ከሌሎች የአፍሪካና የኤዝያ አገሮች ወታደራዊ ተቋማት በሚበልጥ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበረና ለአንዳንድ አገሮችም የስልጠና ዕድል ከፍቶ እንደነበር በህይወት ኖረው የሚመሰክሩ ብዙዎች ናቸው።

ሰራዊቱ ሲመሰረት በቅድሚያ የአገሩን ዳርድንበርና ነጻነት ለማስከበር ቢሆንም ለመሪዎቹ ታማኝ ሆኖ ለማገልገልም ባንዲራ ጨብጦ በመማል ቃል ገብቷል። ይህ የገባው ቃል ግን መሪዎቹ የተሰጣቸውን አደራ ዘንግተው አላፊነታቸውን በሚገባ ለመወጣት ሳይችሉና ይባስ ብለውም በሕዝቡ ላይ በደልና ግፍ ሲፈጽሙ አያገባኝም ብሎ ለሕዝቡ ጀርባውን አልሰጠም።ከገባው ቃል ኪዳንና ዓላማው ጎን ለጎን የወገኑን በደል ለማዳመጥና ብሶቱን አሶግዶ መብቱን ለማስከበር በተደጋጋሚ የተቃውሞ ድምጹን አሰምቶ ከህዝቡ ጎን ተሰልፏል።የመሪዎች ብቻ ሳይሆን የሕዝብ አገልጋይና አካል መሆኑንም በተግባር አሳይቷል።

በእኛ ዕድሜ የምናውቀው የ1953 ዓ.ም. የታህሳስ ወር በነጀነራል መንግስቱ ነዋይና አበሮቻቸው የተካሄደው ወታደራዊ ጸረ ዘውድ አገዛዝ እንቅስቃሴ ለ1966ቱ የየካቲት ሕዝባዊና ወታደራዊ እንቅስቃሴና ለውጥ የፋና ወጊ መሆኑ አይካድም።በነዚህ በአስራ ሶስት ዓመት ልዩነቶች የተካሄደው ወታደራዊ አመጽና እንቅስቃሴ ሕዝባዊ መልክ ቢኖረውም ሕዝቡን ለሚፈልገው ነጻነትና እኩልነት አላበቃውም።ለተጠናከረ የግፍ አገዛዝ ዳረገው እንጂ!ምንም እንኳን የየካቲቱ የሕዝቡም ሆነ የመለዮ ለባሹ ፍላጎትና ትግል በጥቂት አምባገነኖች ቢቀለበስም፣የሕዝቡም ሆነ የመለዮ ለባሹ ትግል ሊቆም አልቻለም።በአምባገነኑ የደርግ ስርዓት ላይ ተደጋጋሚ ተቃውሞና የግልበጣ ሙከራዎች ተካሂደው ሳይሳኩ ቢቀሩም ወታደሩ እጁን አጣጥፎ እንዳይቀመጥ ከሕዝቡ ጎን እንዲቆምና እንዲታገል የሚቀሰቅስ መልእክት ጥለውለት አልፈዋል።

በየወቅቱ የሚነሱ መሪዎችም ሆኑ ስርዓቶች ለዘላለም በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ የማያደርጉትና የማይሞክሩት ነገር የለም፡፤ሕዝብን በመከፋፈል፣መለዮ ለባሹ እንዳይግባባና ሕዝባዊ አመለካከት እንዳይኖረው በጥቅም በመደለልና በቅጣት በማስፈራራት መሳሪያቸው ሆኖ እንዲቀር ይጥራሉ።ጥረታቸው ግን ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታ የለውም፤ የሕዝብ ቁጣ ገደቡን ሲያልፍ የሚበግረውና የሚያግደው ጦር አይኖርም።ስርዓቱ የሚመካበትም ጦር ሃይል፣ከሕዝብ አብራክ የወጣ፣ በችግርና ለኑሮ ሲል በሙያው የተሰለፈ እንጂ ሰብአዊነት የጎደለው፣ የዜግነት ስሜት የሌለው አውሬ ፍጡር ስላልሆነ ከሕዝቡ ጎን ይሰለፋል፤ ይህንንም በአገራችንም ሆነ በሌሎች አገሮች ያየነው እውነታ ነው።
ማንኛውም ስርዓት ዘለዓለማዊ አይደለም። አንድ ስርዓት ተወግዶ በሌላ ሲተካ ፣ለነበረው ስርዓት አገልጋይና እንዳይወድቅ ሲታገልና ግፍ ሲፈጽም የነበረው በሃፍረት የሚሸማቀቅበትና ለፈጸመው ግፍ በሕግ የሚጠየቅበት፣ለሕዝብ መብት መከበር ሸንጡን ገትሮ የተከራከረ፣አሻፈረኝ ያለና ለሕዝባዊ ስርዓት የታገለ በኩራት የሚራመድበት ጊዜ እንደሚመጣ በታሪክ አይተናል።

ለስርዓቱም የሚገሉ እንዳሉ ፣ለሕዝብ ልዑላዊነት የሚታገሉና የሚሞቱ ይኖራሉ።በቃን ሰለቸን ሳይሉ፣ህይወታቸውን አሳልፈው የሰጡ መለዮ ለባሾች ብዙዎቾ ናቸው።ከፍተኛ ማዕረግ የነበራቸውና ለከፍተኛ ማዕረግ የታጩና የሚበቁ ወጣት መለዮ ለባሾች የራሳቸውን ኑሮና ጥቅም ሳይመለከቱ የአገራቸውንና የወገናቸውን ጥቅምና ክብር በሚያረጋግጠው የትግል አቅጣጫ ግዳጃቸውን ፈጽመዋል፤ለመፈጸምም የተዘጋጁ መኖራቸው አይካድም።ለጨቋኝ ስርዓትና መሪዎች አጋር፣ደጋፊና አገልጋይ መሆን የኋላ ኋላ የሃፍረት ማቅ የሚያከናንብ ሲሆን ለአገር አንድነትና ለሕዝብ መብትና ልዑላዊነት መቆም በታሪክ የኩራት ካባ

ያጎናጽፋል።

ለሕዝብ መብት መቆም ሲባል ለራስ፣ለቤተሰብ ፣ለልጅና የልጅልጅ መብት መቆም መሆኑ መታሰብና መታወቅ አለበት።ያን አይነት ስርዓት ሲሰፍን አንደ ግል ዕቃ የሚያሸከረክሩትና የሚያዙት መለዮ ለባሽ አይኖርም።በሙያው ኮርቶና ተከብሮ፣በወገኖቹ ተወዶ የሚኖር መለዮ ለባሽ ይሆናል።ለዚያ ለሙብቃት የሚመኘው መለዮ ለባሽ ሰልፉን ከሕዝቡ ጋር ማድረግ ይገባዋል።ትጥቅና ቀለቡ ሕዝቡ ከሚከፍለው ቀረጥና ግብር እንጂ መሪዎቹ ከኪሳቸው አውጥተው የሚሰጡት ገጸበረከት እንዳልሆነ ሊረዳው ይገባል።

መሪዎች ባይኖሩ አገርና ሕዝብ ይኖራል፣ለዚያም የሚሆን ወታደራዊ ተቋም ይመሰረታል፡፤የጨቋኖች ስርዓት ማክተም ማለት ወታደራዊ ተቋም አከተመ ማለት አይደለም።ስለሆነም የሚያገለግሉት ጨቋኝ ስርዓት ከሌለ እኔም አልኖርም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው።

የኑሮ ግዴታ ሆኖብህ፣ አገርህን ለማገልገል አስበህ መለዮ ለባሽ የሆንክ ዜጋ ሁሉ! ከሕዝብ የተለዩ ፍላጎት እንደሌለህ ይታወቃል፤ አንተም በሰላም፣ መብትና ነጻነት በተከበረበት አገር የመኖር ፍላጎት አለህ፤ ልጆችህም በተሻለ ኑሮና አገር ተወልደው እንዲያድጉና ለቁም ነገር እንዲበቁ ምኞት አለህ፤ እነዚህን ምኞቶችና ፍላጎቶች ለማግኘት ግን አምባ ገነን ስርዓትና መሪዎችን ማሶገድ ይጠይቃል። ሕዝቡ ለነዚህ የጋራ መብቶች በሚታገልበትና መስዋእት በሚከፍልበት ጊዜ ከዳር ቆመህ አትመልከት፣ ወይም የግፈኞች መሳሪያ ሆነህ ለማፈን አትሰለፍ። የሕዝቡ የወደፊቱ እጣ ፈንታ የአንተም ጭምር ነው። እንደምትሸከመው መሳሪያ እንደልባቸው ሊያወጡህና ሊያወርዱህ የሚችሉት አትሁን።አንተም ተቃውሞ አሰማ፤ ከሕዝቡ ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘህ የተሻለች አገር፣ ለወደፊቱ ትውልድ ለማስረከብ ተነሳ። እንዳለፈው ጊዜ መለዮ የለበሱ አምባገነኖች እንዳይጠቀሙብህም ከሕዝቡ ጋር ምከር፣ ሕዝባዊ ስርዓት ለማስፈን የሰለጠነ ፖለቲካ ትግል ከሚያካሂዱት አገር ወዳዶች ጋር ተባበር።

የተሰለፍክበት ዓላማ ከውጭ ወራሪ ሃይል የአገርህን አንድነት፣ ሰላምና ዳርድንበር ለማስከበር ሆኖ ሳለ በስልጣን ላይ የተቀመጠው የውስጥ ጠላት የአገርህን ድንበር ለባእዳን በፈቃደኛነት አሳልፎ እየሰጠና እየቸበቸበ አንተን ከተግባርህ አግዶሃል። ለአገርህ ከምትሰለፍ ይልቅ በውጭ አገሮች የእርስ በርስ ግጭትና የዘራፊዎች ጥቅም የማስከበር ዘመቻ በሰላም አስከባሪ ስም እየተላክ ደምህን እንድታፈስ አድርጎሃል። አንተንም እንደመሬቱ የጦር ሜዳ ሸቀጥ አድርጎ ለዋልክበት ግዳጅ በብዙ ሚሊዮን ብር እየሰበሰበ አንተንና ቤተሰብህን ግን ለችጋር አጋልጧል። የክፍያውን የአንበሳ ድርሻ ባለስልጣኖቹ ሲያግበሰብሱ ላንተ የሚደርስህ ግፋ ቢል የድመቷ እንደሆነ እወቅ። የምታገለግለው ስርዓት በክልልና በጎጥ አደረጃጀት አሰልፎህ እርስ በርስህ እንዳትተማመን፣ ለአገርህ በጋራ እንዳትቆም፣ ብሔራዊ ስሜትህና የአገር ፍቅርህ እንዲላላ በማድረግ ለወደፊቱ ለባሰ ችግርና የእርስ በርስ ውጊያ እንዳዘጋጀህ ተረዳ። እንዳለፉት የጦር ሃይል ባልደረቦች የግፍ አገዛዝን ባለመቀበል እምቢ አልገዛም! ብለህ ተነሳ። በዘንድሮውም የካቲት ወር የዛሬ አርባ ዓመቱን የካቲት የሕዝቡንና የጦር ሃይሎችን ጸረ ፊውዳል ትግል በመዘከር ጸረ አንድነትና ጸረ ኢትዮጵያ የሆነውን በስልጣን ላይ የተቀመጠ ቡድን ለማስወገድ ክንድህን አንሳ!

በስለላና በአፈና ላይ የተሰማራችሁትም ጥሪውን ስሙ። ዛሬ የምትሰልሉለት፣ የምታፍኑለት፣ የምትገሉለት ስርዓትና አምባገነን ቡድን ነገ ሲወድቅ ለመከራ እንደምትጋለጡ አትርሱት። መሪዎቹ የራሳቸውንና የቤተሰባቸውን ህይወት ለማትረፍ እንጂ ለእናንተ የወደፊት እጣ ፈንታ አይጨነቁም። እናንተ ሞታችሁ እነሱ ቢኖሩ ይመርጣሉ። እናንተ ደግሞ እነሱ ተወግደው ከሕዝብ ጋር በሰላምና በነጻነት ለመኖር የሚያበቃችሁን መንገድ ምረጡ። እያንዳንዳችሁ ግደል ሲሉህ አትግደል፣እሰር ሲሉህ አትሰር፣አፍን ሲሉህ አታፍን፣
ሰልል ሲሉህ አትሰልል። የምትገለው፣ የምትሰልለው፣ የምታፍነው፣ የምታስረው፣ የምታሳድደው እንዳንተው ኢትዮጵያዊ ነው፤ እንዳንተው በሰላም ሰርቶ ማደርን የሚሻ ዜጋ ነው። ለጊዜያዊ ጥቅም ብለህ አውሬ አትሁን። ነግ በራሴ ብለህ ወደ ልቦናህ ተመለስ። የነገዋ የተሻለችው፣ የሕዝብ መብትና ነጻነት የተከበረባት ዴሞክራሲያዊቷ ኢትዮጵያ የአንተም፣ የልጅህና የልጅልጅህም ነች። ለዛች አብረህ ለመታገል ቁረጥ።

በአንድነት ለአንድነት ለእኩልነትና ለሕግ የበላይነት እንታገል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ(ሸንጎ)

# አጫጭር ዜናዎች

## የባህርዳር ሕዝብ የተቃውሞ ድምጹን አሰማ

## ለብአዴን/ኢህአዴግ አስደንጋጭ ማስጠንቀቂያ በአደባባይ አስተላለፈ




የባህርዳር ሕዝብ የካቲት 16 ቀን 2006 ኢ.ም ባካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ የአማራ ክልል መንግስት እና ኢህአዴግ ከስልጣን እንዲወርዱ በመጠየቅ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አደረገ።

ሕዝህ የሚያንቋሽሹ፣ የሚያዋርዱ፣ የሚያፍኑ መሪዎች በሙሉ ከስልጣን እንዲወርዱ ብሎም ለፍርድ እንዲቀርቡ የከተማዋ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ ጥያቄ በማቅረብ ለአማራ ክልል ገዝዎችና ለኢህአዴግ አገዛዝ እስደንጋጭ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈ።

ሰላማዊ ስልፉን የጠሩትና ያስተባበሩት አንድነትና መኢአድ

ፓርቲዎች ሲሆኑ ፓርቲዎቹ ጥሩ የሚባል የትብብር ትግል ጅማሬ ማሳየታቸው ታውቋል። በሁለቱ ፓርቲዎች የተጠራው የሰላማዊ ሰልፉ መስረታዊ ጥያቄም የአማራን ሕዝብ የተሳደቡና ያዋረዱ የክልል መሪዎች ከስልጣን ወርደው ለፍርድ እንዲቀርቡ ለመጠይቅ ሲሆን ህዝቡም በገዥዎቹ በመሰደቡ ተቃውሞውን በከፍተኛ ቁጣ አሳይቷል።

በባህርዳር ከተማ የተመመው ሰልፈኛ "የሰደቡን፣ ያዋረዱን፣ የተሳለቁብን ገዥዎች ከስልጣን ይውረዱ"፣ "ኢህአዴግ በቃን ከስልጣን ወረድ" የሚሉ መፈክሮችንና "እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም" በማለት በጋራ መዝሙርና በተለያዩ መፈክሮች ወጣት፣ አዛውንት፣ ልጅ ያዘሉ ሳይቀሩ አደባባይ በመውጣት በአገዛዙ የተሰማቸውን ቅሬታ ገልጸዋል።

የሰላማዊ ሰልፉን ጥያቄ የአማራ ክልልም ሆነ በፌደራል ደራጃ የሚገኙ ባለስልጣናት የሰጡት ምላሽ የለም። በለላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵ ህዝብ ያጋራ ትግል ሸንጎ በህርዳሩን ሕዝባዊ ሰልፍ ከጥንሡ ጀምሮ ድጋፉን ከመስጠቱም በላይ ሌሎች ድጋፋቸውን እንዲሰጡ በመግለጣ መጠየቁ የሚታወቅ ነው።

## ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮ-ሱዳን ድንበር ጉዳይ ላይ የሰጡትን መግለጫ ውድቅ ነው ተባለ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማሪያም ደሳለኝ ሰሞኑን ስለ ኢትዮ-ሱዳን ድንበር የሰጡትን መግለጫ በተመለከተ " የሸፍጥ ክርክር የሀሰት ክምር የታሪክን እውነታ አይቀይርም " በሚል የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቲ ባወጣው መግለጫው የጠቅላይ ሚኒስትሩን ንግግር ውድቅ አደረገ ።

የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው በቅርቡ የኢህአዴግ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር የሆኑት አቶ ሀይለማሪያም ደሳለኝ የሁለቱን ሀገራት የደንበር አወሳሰን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ "ያለፉት የኢትዮጵያ መንግስታት በሻለቃ ግዌን መስመር ተስማምተዋል፣ የእኛም መንግስት ይህንኑ ትከትሏል" በማለት የሰጡት መግለጫ የተጣመመ መሆኑን በመጥቀስ የሻለቃ ግዌን የወሰን ክልል አከላለል ኢትዮጵያን ያላሳተፈ፣ በራሱ ብቻ የተደረገና በዳግማዊ ሚኒሊክና በእንግሊዝ መንግስት መካከል የተደረገውን መሰረታዊ ውል የማያንጸባርቅ በመሆኑ የግዌን መስመር እንደ ሁለቱ ሀገራት የወስን ድንበር ውል የሚቆጠር አይደለም፤ ካሁን በፊት የነበሩ የሀገሪቱ መንግስታትም ይህን የግዌንን መስመር አልተቀበሉም ሲል የሚኒስትሩን መግለጫ አብጠልጥሎታል።

የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በዚሁ መግለጫው በተጨማሪ ያነሳው ጉዳይ የወያኔ ኢህአዴግ መንግስት በድብቅ የመሰረታቸው የኢትዮጵያ ሱዳን የጋራ ድንበር ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ ሱዳን የፖለቲካ ኮሚቴ የሚባሉትን ይፋ ያደረገው ሚስጢሩ አደባባይ ከወጣ በኋላ መሆኑን እንደማስረጃ በመውሰድ አሁንም የሀገሪቱን ሉዖላዊነትና የህዝቡን ጥቅም የሚጋፉ ውሎች መፈጸማቸውን የሚያረጋግጡት ሱዳናዊያን መሆናቸው በኢህአዴግ በኩል የሚነገሩት እውነታ የራቃቸው መግለጫዎች ናቸው ሲል ይገልጣል።

ኮሚቴው በመቀጠልም "የኢትዮጵያን ህዝብ ንቃችሁ ከሱዳን መንግስት ጋር በድብቅ የምታደርጉት ውል ህገወጥ፣ የአገርን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥና እናንተንም በሀገር ክህደት ትግባር የሚያስጠይቅ ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን ከወዲሁ ያሳውቃል" ሲል ለአገዛዙ ግልጽ መልክት አስተላልፏል።

## ሸንጎ የኢትዮጵያን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት እየተካሄደ ያለውን ሸፍጥ የሚቃወም የህዝብ ፊርማ ማሰባሰብ ጀመረ

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት የሀገሪቱን መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠ ስምምነት ላይ መድረሱን በመቃዎም ለተባበሩት መንግስታት የሚቀርብ የህዝብ የተቃውሞ ፊርማ ማሰባሰብ መጀመሩ ታወቀ።

ሸንጎ ይህን በተመለከተ ባወጣው መግለጫ ይህ ሴራ የሚካሄደው ህዝብን በማይወክል ጠባብ ቡድን በመሆኑ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጀርባ የሚፈጸመውን ማንኛውንም ውል እንደማይቀበል ገልጦ፣ ይህ ተቃውሞውም ካሁኑ እንዲታወቅለት ለተባበሩት መንግስታት፣ ለአፍሪካ ህብረት እና ለሌሎችም አለም አቀፍ ድርጅቶችና መሪዎች የሚቀርብ የተቃውሞ ፊርማ በማሰባሰብ ላይ መሆኑን አስታውቋል።

ህዝባዊ ፊርማው እዚህ ይገኛል፡

## "የግፍ አገዛዝን ጠግኖ መቀጠል አይቻልም" ሲል ሸንጎው መግለጫ አወጣ

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ የግፍ አገዛዝን ጠግኖ ለማቆየት አይቻልም በሚል ባወጣው መግለጫ በአንድነት ፓርቲ ዋና ጸሃፊነት ሲያገለግሉ የነበሩትና የፓርቲው አጋፋ የአመራር አባል በአቶ አስራት ጣሴ ላይ የተወሰነውን እስር አወገዘ። ለአቶ አስራት መታሰር ምክንያት የሆነው ህወሓት/ኢህአዴግ አኬልዳማ /የደም መሬት በሚል ያስተላለፈውን ፕሮፖጋንዳ በመተቸታቸው መሆኑ በመጥቀስ፣ የመናገርና ሀሳብ የመግለጽ ነጻነት እንደታፈነ እየቀጠለ መሆኑን የሚያሳይ ሌላው ማረጋገጫ ነው ብሏል።
በሌላ በኩል " የህዝብን የነጻነት ፍላጎት አፍኖ እስከ መጨረሻ መቆየት አይቻልም " በሚል ሀይለ ቃል በአርና ትግራይ ላይ የሚደረገውን ወከባ በጥብቅ አውግዟል። ሸንጎው በአማራው ህዝብ ላይ ያነጣጠረውን የዘር ጥላቻ ቅስቀሳ የሚያወግዝም መሆኑን በየካቲት መጀመሪያ ላይ ባወጣው መግለጫ አስታውቋል።

Website: http://www.ethioshengo.org

Email : shengo.derbiaber@gmail.com
Shengo.pr@ethioshengo.org

Tele: 44 793 760 0756
1 916 848 6790